# *<u>በሲያትል የኢትዮጵያውያን ፎረም ይመሰረታል!!</u>*

<u>ከሰውለሰው (ግንቦት 2003 ዓ.ም)</u>

በአንድ ወቅት መለስ ዜናዊ እነ አባዱላ ገመዳን ሰብስብቦ "እያንዳንዱ ኦሮሞ እንደፈጣን ሎተሪ ልቡ ቢፋቅ ኦነግ ነው" ብሎ ተቆጣ  ሲባል ሰምተን ነበር።መለስ ዜናዊ ህወሃት የተባለ የአንድ ብሄር ድርጅት መሪ ነው።ይሄ የእርሱ የማይገሰስ መብት ነው።አባዱላ ገመዳ ግን ከኦህዴድ ውጭ ሌላ መሆን አይችልም።ሌሎችም ኦሮሞዎች ከኦህዴድ ውጭ ሌላ የሚወዱትን የሚፈልጉትን እንሆናለን ቢሉ ወዮላቸው።የኦሮሞ ልጆች የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን መደገፍ ወይም የድርጅቱ አባል የመሆን መብት እንዳላቸው መለስ ዜናዊ አያውቅም ማለት አይቻልም።የመለስ መላ ምት ግን የኦሮሞ ልጆች የፈለጉትን መሆን አይችሉም ከሚል ትእቢት የመነጨ ነው።ይሄን የተቃወሙ የኦሮሞ ልጆች ለእስር፤ለግድያ እና ለስደት ተዳረጉ።ከነ አቶ መለስ ዜናዊ የግድያ ቡድን አምልጠው ከተሰደዱት የኦሮሚያ ልጆች መካከል ጄኔራል ከማል ገልቾን ብንጠቅስ በቂ ነው።አንድ ጄኔራል ለመፍጠር አገሪቷ ብዙ መዋእለ ንዋይ ታጠፋለች።ብዙ መዋእለ ንዋይ የወጣበት ጄኔራል ከማል ገልቾ  ስደተኛ ሆኖ  ኤርትራ የምትባል አገር ውስጥ ይኖራል አሉ።

ከዚያም ሳሞራ የኑስ የተባለው የመለስ ጦር አበጋዝ የአማራ  ብሄር አባል የሆነውን ኮሬኔል አለበል አማረን ቢሮው ጠርቶ "ስማ አባቶችህን አርቀን ቀብረናቸዋል የቀራችሁትን እናንተንም ቢሆን ገና እንቀብራችኋለን" ሲል ዛተ።ኮረኔሉም ከመሞት መሰንበት ብሎ ቤተሰቦቹንና አገሩን ጥሎ ጄኔራል ከማል ገልቾ ወደ ተሰደደበት ኤርትራ ገባ።ሁሉቱ የአገሪቷ ልጆች ቤተሰቦቻቸውንና አገራቸውን ጥለው በስደት ላይ ይገኛሉ።እንደነርሱ ብዙ ሺዎች እንዳሉም እናውቃለን።

አስቀድሞ ኦሮሞው ከማል ገልቾ ሲሰደድ በወቅቱ ለመለስ ዜናዊ ሲሰራ የነበረው አማራው ኮሬኔል አለበል አማረ ምን አንዳለ አናውቅም።የምናውቀው አንድ ነገር ብቻ ነው።ሁለቱም የታላላቁ ብሄር አባሎች ተራ በተራ ለጥቃት ተጋልጠው ካገራቸው መሰደዳቸውን።በአንድ ዙር ኦሮሞ ይቀጠቀጣል በሚቀጥለው ዙር ደግሞ የአማራው ተራ ይሆናል።በዚህ ግዜ ውስጥ "ነግ በእኔ" የሚባለው አባባል የት አባቱ እንደገባ አናውቅም።አንዱ ሲቀጠቀጥ ሌላው እያየ ዝም የማለቱ ውጤት መጨረሻው የሁሉቱም መጎዳት ሆነ።

መለስ ዜናዊ 'የብልህነቱ' ጥግ አማራንና ኦሮሞን መከፋፈሉ ነው ይባልለታል።ይህ እንዴት ብልህ ሊያሰኝ እንደሚችል መለስ ዜናዊ ብቻ ያውቃል።እነዚህ ሁለቱ ትላልቅ ብሄረሰቦች በጠላትነት ተፋርጀው እርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ባይገቡለትም ተባብረው እንዳይቆሙ ለማድረግ በብርቱ ሥርቷል። መለስ ግድ የለውም ወደ ጎንደር ጎራ ካለ ኦሮሞ ሊበላህ እየመጣ ነው ብሎ በአደባባይ ለመናገር በሰማይ ያለውን እግዜርን አይፈራም።እግር ጥሎት ወደ ወለጋ ብቅ ካለ ደግሞ ነፍጠኛ አማራ ሊያጠፋህ እየመጣ ነውና ተጠንቀቅ ማለቱን አይረሳውም።እንዲህ በሰው ልጆች መካከል ጥርጣሬንና አለመተማመንን ሲዘራ የሚኖርን ሰው  አጃቢዎቹ በምን መለኪያ "ብልሁ" መሪ እያሉ እንደሚያሞካሹት ስናስብ እንገረማለን።

እንዲሁም ወደ ትግራይ በሄደ ግዜ "አንተ እኮ ወርቅ ህዝብ ነህ እንኳንም ካንተ ወርቅ ከሆንከው ህዝብ ተወለድኩ" ካለ በኋላ "አማራና ኦሮሞ ግን ደርጎች ስለሆኑ ከነዚህ ጠላቶችህ እጅ ከህወሃት/ከእኔ በቀር የሚያድንህ የለም" ብሎ መስበኩን አይተውም።እንዲህ የሚያድረገው ግን የትግራይን ህዝብ ስለሚወድ አይደለም።የትግራይን ህዝብ አብሮ ከኖረው ህዝብ  ገንጥሎ የግሉ ንብረትና ዋሻው አድርጎ ሁሉንም ቅጥቅት አድርጎ እስከ ልጅ ልጆቹ መግዛት ስለሚፈልግ ነው።

እንደ እኔ እምነት ማንም የማንም ጠላት አይደለም።ሁላችንም ኢትዮጵያ የምትባል ድሃ አገር ልጆች ነን።በዚህች ኢትዮጵያችን ውስጥ ህዝብ ለህዝብ ጠላት ሁኖ አያውቅም።እረ የትም አገር ህዝብ የህዝብ ጠላት ሁኖ አያውቅም።ኢትዮጵያ ውስት ጠላት አለ ከተባለም የሚኖረው ጠላት አሁን በስልጣን ላይ  ያለው "መንግስት" ብቻ ነው።በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መንግስት የተባለ አካል ለህዝብ ጠላት ሁኖ ሲቀመጥ ህወሃት የመጀመሪያው ነው።ከዚህ ቀደም በነበሩ መንግስታት ብዙ በደሎች መፈጸማቸውን እናውቃለን።የቀደሙት "መንግስታት"አንድ አምባገነን መንግስት የሚያደርገውን ክፍ ነገር ሁሉ ፈጽመዋል።ወያኔ ግን  መንግስት ያደርገዋል ተብሎ የማይጠበቀውን ክፍ ነገር በአገሪቷ ላይ በማድረሱ የህዝብ ጠላት ሁኖ ቁጭ ብሏል።

ባለፍት ታሪካችን ውስጥ ጭንቅላታችንን ይዘን ኡ ኡ እንድንል የሚያሰኙን አስቀያሚ በደሎች መፈጸማቸው እውነት ነው።ይህን ሲባል ግን አያቶቻችን ያደረጉት መልካም ነገር የለም ማለት አይደለም።ቆመን ልናወድሰው የሚገባን አኩሪ ገድል መፈጸማቸውን የሚረሳ ሂሊና ሊኖረን አይገባም።በብዙ ሊወደሱ የሚችሉ መልካም ታሪኮች እንዳሉን ሁሉ ብዙ ደግ ያልሆኑ ነገሮችም አሉ።ደጉንም ክፍውንም የፈጸሙት ግን ኢትዮጵውያን ነበሩ።እነዚህ ሰዎች ሌላ የሚታወቅ አገር አልነበራቸውም።አገራቸው ኢትዮጵያ ነች።በዚህች አገር ውስጥ ተበድያለው የሚል ህዝብ አለ።ይህን በደል ቁጭ ብለን ማዳማጥ አለብን።ራሳችንንም ተበድያለው ከሚለው ሰው ቦታ ላይ አስቀምጠን ነገሩን መመርመር አለብን።ሰው ተበድያለው ካለ አልተበደልክም ብሎ ሙግት መግጠም ፍቅርን ያቀዘቅዛል።ብዙ ሰዎች ዛሬ ላይ ሁነን መቶ ዓመት ወደ ኋላ ስንመለከት ከደጉ ነገር ይልቅ ክፍው ነገር ጎልቶ እየታየን ችግር ውስጥ ገብተናል።ይሄም አስተያየት ሚዛኑን ቢጠብቅ ለሁላችንም ይጠቅማል።ብዙ በደል  ዛሬ ሞልቶልን እያለ መቶ ዓመት ወደ ኋላ ሂደን ተጨማሪ በደል ፍለጋ መኳተናችን ዛሬን በጥሩ ሁኔታ እንዳንኖር ደንቃራ ሁኖብናል።የነገውንም ተስፋችንን አጨልሟል።መልካም አገር ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ላይም ትልቅ እንቅፋት ሁኖ ቆይቷል።በዚህም ምክንያት  እጣ ፈንታችን  ከደስታ ይልቅ ሃዘን የሞላበት፤ከመተማመን ይልቅ ጥርጣሬ የወረሰው፤በፍቅር ዓይን ከመተያየት ይልቅ የጎሪጥ የምንተያይበት እንዲሆን ሁኗል።በደሎቻችን ላይ ማትኮራችን ሚዛንኑ ስለደፋ ለሚመጣው ትውልድ የምንተውለት የእኛን እጣ ፈንታ መሆኑ ግድ ነው።ከልዩነቶቻችን ይልቅ አንድ ሊያደርጉን በሚችሉ በጎ ነገሮች ላይ ግዜያችንን ብናውል ነፍሳችን ሃሴት ታደርግ ነበር።

ወቅቱ ከታሪክ እስረኝነት ራሳችንን የምናስፈታበት ግዜ ነው።ባለፍት በርካታ ዓመታት ውስጥ የታሪክ እስረኛ ሁነን ኑረናል።የታሰርንበት ልዩ ልዩ ሰንሰለት እንዲበጠስ ሁላችንም በአንድ ላይ ቁጭ ብለን አንዳችን የአንዳችንን እስራት ለመፍታት  መጣር  ይኖርብናል።የአማራም፤የኦሮሞም፤የሶማሌም፤የትግሬም፤የጉራጌም፤የወላይታም፤የሲዳማም፤የሌሎቹም ኢትዮጵያዊያን ጥያቄ አንድና አንድ ነው።እርሱም እውነተኛ ነጻነት ነው።ነጻነት ! ነጻነት ! አሁንም  ነጻነት !

እኔ የደቡብ ልጅ ነኝ።የተወለድኩትም ያደኩትም ደቡብ ኢትዮጵያ ነው።እናም ኢትዮጵያ በምትባል በዚያች ውብ አገር ውስጥ ሁላችንም በደስታና በአንድነት የማንኖርበትን ምክንያት ብፈልግ አላገኘውም።ከማውቀው ቋንቋ በተጨማሪ አማርኛን ደህና አድርጌ እንደምናገር ሁሉ ኦሮሚኛን ተምሬ እንደ አማርኛ የማልጠቀምበት ምክንያት የለም።ኦሮሚኛም እንደ አማርኛ የሁላችንም ቋንቋ የማይሆንበት አንዳችም  ምክንያት አይታየኝም።የሚመጣውም ትውልድ ሁለቱን ቋንቋዎች አቀላጥፎ እየተናገረ በሰላምና በደስታ የማይኖርበትን ምክንያት የሚነግረኝ ‘ጥበበኛ’ ይኖር ይሆን ? እንዲህ ያለ ጥበበኛ ቢገኝም ጥበበኛ ሳይሆን ተንኮለኛ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ  ብሄሮች በተለይም ኦሮሞና አማራ አንድ ላይ ተባብረው በፍቅርና በደስታ እንዳይኖሩ ለማድረግ የሚሞክረው መለስ ዜናዊ ብቻ ነው።የዚህ ሰው መጫወቻ ካርድ አንድ ነው።አንዱን ዘር ተበዳይ ሌላውን በዳይ አድርጎ ማቅረቡ።ይህ ሰው በዘር ሰንሰለት ሊያስረን እየሞከረ ነው።እንደሚባለውም የመቶ ዓመት የቤት ሥራ የሰጠን እርሱ ነው እንዴ ? ከሆነም የቤት ሥራው አሁን መፈጸም አለበት።ትርፍ ግዜ ያለን አይመስለኝም።

አዎን ኢትዮጵያ በምትባል አገር ውስጥ ኦሮሞና አማራ አብረው በደስታና በአንድነት መኖር ይችላሉ።እኔም ከእነርሱ ጋር አብሬ ደስ ብሎኝ በአገሬ ኢትዮጵያ መኖር እችላለሁ።ዛሬ ሁላችንም በተለይም አማራና  ኦሮሞ ነጻነታቸውን የሚፈልጉ ከሆነ እርስ በርሳቸው በጥርጣሬ ከመተያየት ተላቀው እጅ ለእጅ የሚያያዙበት ትከሻ ለትከሻ የሚደጋገፍበት ግዜው አሁን ነው።እነዚህ ሁለቱ ብሄረሰቦች አንድ ከሚያደርጋቸው ትልቅ ቁም ነገር ይልቅ በጥቃቅን ልዩነቶቻቸው ላይ በማተኮራታቸው ምክንያት ነጻነታቸውን ተገፍፈው ክብራቸውንም አጥተው ዝቅ ብለው ኖሩ እንጂ ያተረፍት ነገር የለም። በዚህም ምክንያት አገራችንም ኢትዮጵያ ክብሯ ተዋረደ።ግራማ ሞገሷም ጠፋ።ልጆቿም ስደተኞች ሆኑ።

እንዲህ ሲሆን የታዘቡ በሲያትልና አካባቢዋ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን አንድ ነገር እናድርግ ሲሉ መከሩ።እናም ከዚህም ከዚያም ተጠራርተው አስራ አንድ አባላት ያሉት ኮሚቴ መሰረቱና ስሙንም “በሲያትል የኢትዮጵያዊያን ፎረም” በሚል ሰየሙት።ለብዙ ግዜ ሲመክሩ ቆይተው የመጀመሪያውን ህዝባዊ ጉባኤ May 28,2011 ከቀኑ 2፡00 ሠዓት ጀምሮ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አዳራሽ  ለማድረግ ወስነዋል።የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ ውስጥ መሆኑ አሪፍ ምርጫ ነው።ኢትዮጵያ ኮሚኒት እንደ ሌሎች ኮሚንቲ አዳራሾች ሰዓቱ አለቀ ብሎ አያባርረንም።ዋጋም ጨምሩ ብሎ አያስጨንቀንም።ለዚህም የኢትዮጵያ ኮሚኒት አዳራች ጥሩ ምርጫ ነው።

በዚህ እለት ልዩ ልዩ አርቲስቶች ተገኝተው እለቱን ያደምቁታል ተብሎ ይጠበቃል።አማርኛውንም ኦሮሚኛውንም ትግሪኛውንም ሌላ ሌላውንም እንጨፍራለን።በዚያ ማንም ዘራችንን አይጠይቀንም ሁላችንም ኢትዮጵያዊያን ነን።የአንዲት አገር ልጆች።በአማርኛም በኦሮሚኛም በሶማሊኛም በትግሪኛም በሌላም ቋንቋ ስለ ነጻነታችን እንመካከራለን።እነማን ናችሁ የሚለን ሰው ከተገኘም ድምጻችንን ከፍ አድርገን ኢትዮጵያዊያን ነን እንላለን።በዚህም መለስ ዜናዊ መነጽሩን ከፍ ከፍ እያደረገ ጸጉሩን ሲነጭ ይሰነብታል።

ስለዚህ በሲያትልና አካባቢዋ የምትኖሩና የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባናል የምትሉ ሁሉ በእለቱ በመገኘት የበኩላችሁን አስተዋጽኦ አበርክቱ።ልዩነቶቻችንን ለጥንካሬያችን ምንጭ አድርገን እንድንጠቀም ግዜው ግድ ይለናል።ከመለያየት የምናተርፈው ባርነት ብቻ ነው።ተለያይተን የምንፈልገውን ነጻነት የምናገኝ አይመስለኝም።ኑ !! ኑና እጅ ለእጅ ተያይዘን መለስ ዜናዊ ሲሰራልን የቆየውን የጥርጣሬና የጥላቻ ግንብ እናፍርሰው። የኢያሪኮ ግንብ በጩኸት ፈርሷል።እኛም ድምጻችንን ከፍ አድርገን ሁላችንም የአንድ አገር ዜጎች ነን ብለን እንጩህ። ያን ግዜ የጥርጣሬውና የጥላቻው ግድግዳ እንደ ኢያሪኮ ግንብ ይፈርሳል።አበቃሁ።

ነጻነት ለሰው ልጆች ሁሉ ይሁን !!!

እግዚአብሄር አገራችንን ይባርክ !!!

Freeme97@gmail.com